ህዳር 17 ቀን 2002 ዓ.ም

ክቡራትና ክቡራን

የኢትዮጵያ ህዝብ በዴሞክራስያዊ ስርዓት ለመተዳደር ይፈልጋል። ይህን ፍላጎቱን ምርጫ 97 ላይ በግልፅ አስተላለፎአል። ይህንን እያዩ ያለውን መስተዳደር ለሰላሳና አርባ ዓመታት ለማስቀጠል የሚለፉት ወገኖች አሁን ድረስ ከምርጫ 97 ሊወስዱት የሚገባውን ትምህርት በተገቢው አለመውሰዳቸውን ያመለክታል።

ንጉሠ ነገሥቱ አገዛዛቸው ባለበት መቀጠሉ እንደማይቻላቸው ምልክቱን 1953 ዓ.ም ላይ ያገኙት ቢሆንም ከዚሁ ለመማር ባለመቻላቸው ኋላ 1967 ላይ የሆነው ሆነዋል። የኮሎኔል መንግስቱ ኃ/ማርያም መንግስትም በያዘው መቀጠል እንደማይቻለው ያገኛቸው ምልክቶች በርካታ የነበሩ ቢሆንም ከሽሬው ውድቀት በኋላ የተከሰተው የመንግስት ግልበጣ ሙከራ በምሳሌነት መጥቀስ ይበቃል። ይህም ሆኖ መውሰድ የሚገባውን ትምህርት ለመወሰድ ባለመቻሉ 1983 የሆነው ሆኖአል።

ሀገራችን ኢትዮጵያ በእነዚህ ጥቅም ላይ ያልዋሉ ምልክቶች መልካም የለውጥ ዕድሎች ያመለጧትን ያክል ኋላ በሃይል የመጡትን ለውጦች ተከትሎ በመጡት ምስቅልቅሎች አልተጎዳችም ማለት አይቻልም።

የ97 ምልክት ከቀደምት ምልክቶቹ የተለየ የሚያደርገው በጦር መሳርያ ሳይሆን በምርጫ ካርድ የታየ መሆኑን እና መልእክት አስተላላፊዎቹ ጦር መሳርያ ያነገቱት መሆናቸው ቀርቶ ሕዝቡ ራሱ መሆኑን ነው። ምልክቱ መተላለፉ ግን የሚያከራክር አይደለም።

ከገዢው ፓርቲ በኩል እና ከአንዳንደ የዓለም አቀፉ ማሕበረ ሰብ አባላት ዴሞክራሲ ሂደት ነው የሚለውን አባባል በአጽንኦት ሲነገር እና ሲደጋገም እሰማለሁ። ከዚህ በመንደርደር ገዢው ፓርቲ ለሰላሳ እና አርባ ዓመት ልግዛችሁ ታገሱኝ ሲል ሌሎቹ ደግሞ ለኢትዮጵያውን አሁን ያለው አያንሳችሁም የቀረው ቀስ ብላችሁ ትደርሱበታላችሁ ይሉናል።

እንደኔ እምነት ዴሞክራሲ በዕለት ተዕለት ሂወት እየኖሩበት የሚያዳብሩት እና የሚዳብሩበት እንጂ እንዲሁ በአንድ ወቅት ከተፍ የሚል ነገር አይደለም። በዕለት ዕለት ሂወት ካልኖሩበትና ካልተለማመዱበት ሊደርሱበት አይችሉም።

በዚህ ሂደት በጎ ተሩፋት እንደሚኖሩ ሁሉ ስህተቶች ሊፈጸሙና ጉዳትም ሊደርስ እንደሚችል በገነዘብም በዴሚክራስያዊ መንገድ እየተጓዝን እያለን ለናደርግ በምንችለው ስህተት ምክንያት ልንከፍል የምንችለው ዋጋ ዴሞክራሲን በቀጠሮ በማስተላለፍ ወይም ጨርሶ በማሽቀንጠር ልንከፍል ከምንችለው ዋጋ በጣሙን ያነሰ መሆኑን ነው። ያለፈው ታሪካችን ይህንን እውነታ በአጽንኦት የነገረን በመሆኑ ዴሞክራሲን አሁኑኑ እንስራው እና እንኑርበት፤ ቀጠሮ አንስጠው እላለሁ።

ክቡራትና ክቡራን

ኢትዮጵያውያን በዴሞክራስያዊ ስርዓት መኖርን እንመኛለን፤ ለዚህም ሲባል ብዙ መስዋእት ተከፍሎአል። ከተከፈለው መስዋእትነት አኳያ አሁን ድረስ የተመኘነው ሥርዓት ዘንድ ባለመድረሳችን ተስፋ መቁረጥና ራስን ከፖለቲካ የማግለል ሁኔታ ይታያል። የምር ተፎካካሪ የሆኑትን ፓርቲዎች መቀላቀል ራስን ለአደጋ እንደማጋለጥ ተደርጎ የሚቆጠርበት ሁኔታም አለ።

በዚህ አገር ጠንካራ ተፎካካሪ ፓርቲ ሆኖ ለመዘለቅ ያለው መንገድ መሰናክል የበዛበት መሆኑ ቢታወቅም ካለ ጠንካራ ተፎካካሪ ፓርቲ ዴሞክራሲ መገንባት

ጠንካራ ፓርቲ የመሆን ሰፊ እድል ያለውን ፓርቲ እውን ጠንካራ ፓርቲ እናደርገዋለን የሚል ሙሉ እምነት አለኝ።

ክቡራትና ክቡራን

የኢትዮጵያ ፖለቲከኞች የኢትዮጵያ ሕዝብ ለዴሞክራሲያዊ ስርዓት እውን መሆን ያለውን ምኞትና ተስፋ ከግብ ለማድረስ ደፋ ቀና ማለታቸው አልቀረም። ይህ እውን እንዲሆን የምንመኝ ዜጎች መገንዘብ ያለብን የመጀመርያው እውነታ ዴሞክራሲ በአንድ ፓርቲ ስርዓት የማይገነባና መድብለ ፓርቲአዊ ስርዓት ግድ እንደሚል ነው። መድበለ ፓርቲያዊ ስርዓት መኖሩ አንድ አስፈላጊ ሁኔታ ቢሆንም በአገራችን 92 የተመዘገቡ ፖለቲካዊ ፓርቲ አሉ መባሉ ለአንድ ፓርቲ አገዛዝ የተመቸ ሁኔታ መኖሩን ያመለክት እንደሆነ እንጂ የምር መድብለ ፓርቲያዊ ስርዓት መኖሩን አያመለክትም። ከዚህ መሳቅያነት ወጥተን በቁጥር አነስተኛ የሆኑ ጠንካራ ተፎካካሪ ፓርቲዎች ወደ ሚኖሩበት የመሸጋገር ሥራ ይጠብቀናል።

በአንድ አገር በቁጥር አነስተኛና ጠንካራ ተፎካካሪ ፓርቲዎች መፈጠራቸው የአገሪቱ ልሂቃን እና ፖለቲከኞች ግለ ስብ ወይም ቡድን ከመሆን ተሻግረው ራሳቸውን ለአገር እና ከአገራዊ ጥቅም የማስገዛታቸው፤ እንደፖለቲከኞችም የማደጋቸውና የመስከናቸው ምልክት ነው። በሚገባ ታስቦበትና ተመክሮበት የተሰራ ሲሆን ደግሞ በመሰረታዊ ሃገራዊ ጉዳዮች ላይ የመቀራረባቸው እና የመግባባታቸው ምልክት ነው።

መድረክን የጀመርነው የኢትዮጵያን ችግሮች ከትብብር ውጪ አንድ ፓርቲ ብቻውን ሊፈታቸው የማይቻለው መሆኑን ከመገንዘብ እንደመሆኑ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራስያዊ አንድነት መድረክ እውን ከሆነ በኋላም ቢሆን ቀጣይ እምርታዎች የሚጠበቅበት በሂደት ላይ ያለ ፕሮጀክት መሆኑ ሊጤን ይገባዋል። እኔ አንድነትን ስቀላቀል መድረክንም መቀላቀሌ እንደሆነ፤ አንድነትን ማጠናከር መድረክንም ማጠናከር መሆኑን ከመገንዘብና ሁላችን እጅ ለእጅ ተጨባብጠን በምናደርገው የጋራ ትግል ሃገራዊ ፕሮጀክቱን በማሳካት የኢትዮጵያ ህዝቦች ተስፋ እናለመልማለን ከሚል እምነት ነው።

መተባበር ሂደት እንደመሆኑ መውደቅና ከውደቀቱም እየተማሩና እያሻሻሉ እንደገና መነሳት ይኖራል። መተባበር በታየ ቁጥር መፍረሱ አይቀርም ለሚሉት ትንቢት ተናጋሪዎች ሂደቱ ችግር የተሞላበት ለመሆኑ የማንከራከረውን ያክል ለውጤት እንደሚበቃ ግን የማንጠራጠር መሆናችንን ልንገልፅላቸው እንወዳለን።

በዚሁ አጋጣሚም ኢትዮጵያ ዴሞክራስያዊ ስርዓት እንዲኖር ከምር የሚመኙና የሚታገሉ በበርካታ ፓርቲዎች ተበታትነው ያሉት ኢትዮጵያውያን ከሌሎች ወገኖቻቸው ጋር ተባብሮ ለመስራት በመወሰን በኢትዮጵያ ዘጠና ሁለት ፓርቲዎች አሉ የሚለውን አሳፋሪ ዜና ታሪክ እንዲያደርጉት በአክብሮት እጠይቃቸዋለሁ። አለመተባበር የአምባገነኖችን የስልጣን ዘመንንና የሕዝባችንን ስቃይ ያራዝማል፤ መተባበር ግን የዜጎችን ሰብአዊና ዴሞክራሲ መብቶች መከበርን የሕግ የበላይነትን የነፃ እና ገልልተኛ ተቋማት መኖርን ያቀላጥፋል። ስለ ህግ የበላይነት ሳስብና ስናገር ወትሮውን ወደ ኅሊናየ የምትመጣው የአንድነት ሊቀ መንበር ወ/ሪት ብርቱካን ሚዲቅሳ ናት። በእርሷ ላይ በደረሰው ዳግም እስር በተለያዩ አጋጣሚዎች እና መድረኮች እንደተናገርኩት ሁሉ ለዜጎች ነጻነት እና ለሕግ የበላይነት የምንቆም ሁሉ ለእርሷና መሰል የኅሊና እስረኛ ወገኖቻችን መፈታት በጋራ እንቁም እንተባበር! እንተባበር! እንተባበር! እላለሁ።

አመሰግናለሁ

ስዬ አብርሃ

አዲስ አበባ

ህዳር 17 ቀን 2002 ዓም